የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ገንዘብ ቢሮ

የታክስ ወኪልነት ፍቃድ አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ

መመሪያ ቁጥር 172/2018



ነሐሴ 2018 ዓ.ም

ባህር ዳር

መመሪያ ቁጥር 172/2018 ዓ/ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አውጪው ባለሥልጣን

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 135 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2010 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የታክስ ወኪልነት ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 172/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. ትርጓሜ

በአዋጁ ትርጉም የተሰጠው ቃል ወይም ሐረግ በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል። ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል፦

1/ "የታክስ ወኪል" ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 95 መሠረት ፈቃድ የተሰጠው የታክስ ወኪል ነው።

2/ "የታክስ ወኪልነት አገልግሎት" ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ታክስ ከፋዮች ከገቢዎች ቢሮ ጋር ለሚኖራቸው ጉዳዮች ታክስ ከፋዮችን በመወከል ከገቢዎች ቢሮ ጋር ማንኛውንም ዓይነት የሥራ ግንኙነት ማድረግ ነው።

3/ "የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ" ማለት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቃት ያለው ስለመሆኑ በገቢዎች ቢሮ የሚሰጥ የሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ነው።

4/ "የታክስ ወኪልነት ንግድ ሥራ ፈቃድ" ማለት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ መሠረት አግባብ ባለው ፈቃድ ሰጪ አካል የሚሰጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ነው።

5/ "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት የታክስ ወኪሉ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ ምክንያቶች በተወሰነ አካባቢ የተነሣ ወይም የተፈጠረ ጦርነት፣ ቃጠሎ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ጽኑ ሕመም ሲኖር እና ይህም በታክስ ወኪሉ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ ሲኖረው ነው።

6/ "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ነው።

7/ "ደንብ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የታክስ አስተዳደር አዋጅን ለማስፈጸም የወጣ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2010 ነው።

8/ "ሰው" ማለት ግለሰብ፣ የሽርክና ማኅበር አባል ወይም ተቀጣሪ ወይም የኩባንያ ተቀጣሪ ነው።

9/ "ቢሮ" ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ነው።

10/ "የገቢዎች ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ቢሮ ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ መምሪያዎችን፣ ጽሕፈት ቤቶችን እና የቀበሌ ማዕከላትን ይጨምራል።

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 95 መሠረት የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ ለማግኘት ከሚፈልግ ወይም ፈቃድ በተሰጠው ግለሰብ፣ ኩባንያ እና የሽርክና ማኅበር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

የታክስ ወኪልነት የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ እና እድሳት ስለመወሰን

5. የታክስ ወኪልነት የፈቃድ ደረጃዎች

1/ የደረጃ "አንድ" የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማናቸውም ታክስ ከፋይ አገልግሎት ለሚሰጥ ሰው የሚሰጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ነው።

2/ የደረጃ "ሁለት" የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከደረጃ ሀ ታክስ ከፋዮች በስተቀር ለሌሎች ለማናቸውም ታክስ ከፋዮች አገልግሎት ለሚሰጥ ሰው የሚሰጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ነው።

6. የደረጃ "አንድ" የታክስ ወኪል ፈቃድ ለመስጠት ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ

1/ በታክስ አስተዳደር፣ በአካውንቲንግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በማኔጅመንት፣ በሕግ ወይም በሌላ በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ ወይም አቻ የትምህርት ዝግጅት ያለው፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፉት አምስት ዓመታት ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ክትትል ሥር በመሆን የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በመስጠት ወይም እንደ ታክስ ሠራተኛ በማገልገል በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር 4 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያለው፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ገቢዎች ቢሮ ወይም ገቢዎች ቢሮ የታክስ ወኪል ሥልጠና እንዲሰጥ እውቅና የሰጠው ተቋም የሚሰጠውን የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ ለማውጣት የሚሰጠውን የአቅም ማጎልበቻ ኮርስ በብቃት መከታተል እና መግቢያ ፈተናውን ከ50 በመቶ እና ከዚያ በላይ ውጤት ያመጣ እና የምሥክር ወረቀት ያለው፤

4/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተው የሽርክና ማኅበር ከሆነ እያንዳንዱ የማኅበሩ አባል መልካም ጠባይና ሥነ ምግባር ያለው ስለመሆኑ በገቢዎች ቢሮ ሲረጋገጥ፤

5/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተው ኩባንያ ከሆነ እያንዳንዱ የኩባንያው ዳይሬክተር፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሌላ ሥራ አስፈጻሚ መልካም ጠባይ እና ሥነ ምግባር ያለው ስለመሆኑ በገቢዎች ቢሮ ሲረጋገጥ፤

6/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ማለት በታክስ ሠራተኛነት ባለፉት አምስት ዓመታት በአገር ውስጥ ታክስ ጉዳዮች ላይ የሠራ ማለት ነው።

7. <u>የደረጃ "ሁለት" የታክስ ወኪል ፈቃድ ለመስጠት ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ</u>

1/ በታክስ አስተዳደር፣ በአካውንቲንግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በማኔጅመንት፣ በሕግ ወይም በሌላ በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ በዲግሪ የተመረቀ ወይም አቻ የትምህርት ዝግጅት ያለው፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፉት አምስት ዓመታት ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ክትትል ሥር በመሆን የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በመስጠት ወይም እንደ ታክስ ሠራተኛ በማገልገል 2 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያለው፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ገቢዎች ቢሮ ወይም ገቢዎች ቢሮ የታክስ ወኪል ሥልጠና እንዲሰጥ እውቅና የሰጠው ተቋም የሚሰጠውን የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ ለማውጣት የሚሰጠውን የአቅም ማጎልበቻ ኮርስ በብቃት መከታተል እና መግቢያ ፈተናውን ከ50 በመቶ እና ከዚያ በላይ ውጤት ያመጣ እና የምሥክር ወረቀት ያለው፤

4/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተው የሽርክና ማኅበር ከሆነ እያንዳንዱ የማኅበሩ አባል መልካም ጠባይ እና ሥነ ምግባር ያለው ስለመሆኑ በገቢዎች ቢሮ ሲረጋገጥ፤

5/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተው ኩባንያ ሲሆን እያንዳንዱ የኩባንያው ዳይሬክተር፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሌላ ሥራ አስፈጻሚ መልካም ጠባይ እና ሥነ ምግባር ያለው ስለመሆኑ በገቢዎች ቢሮ ሲረጋገጥ፤

6/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ማለት በታክስ ሠራተኛነት ባለፉት አምስት ዓመታት በአገር ውስጥ ታክስ ጉዳዮች ላይ የሠራ ማለት ነው።

8. ለታክስ ወኪልነት ሙያ ብቁ እና ተስማሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ሌሎች መስፈርቶች

ማንኛውም ግለሰብ፣ የኩባንያ ተቀጣሪ፣ የሽርክና ማኅበር አባል ወይም ተቀጣሪ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማግኘት፦

1/ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ እና ዕድሜው ከ25 ዓመት በላይ የሆነ ሰው፤

2/ ከታክስ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ወንጀል በመፈጸሙ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ያልተረጋገጠ፤

3/ የሙያ ኃላፊነት መድኅን ዋስትና ለማስያዝ አቅም ያለው፤

4/ በጽሑፍ ቃለ-መሐላ መፈጸም የሚችል።

9. በታክስ ወኪልነት ሙያ በሽርክና ማኅበር ወይም ኩባንያ ስለመሥራት

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣ 6፣ 7 እና 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ ወኪልነትን በሽርክና ማኅበር ወይም ኩባንያ መሥራት የሚቻለው ከሁለት ያላነሱ የታክስ ወኪሎች ሲኖሯቸው ብቻ ነው፤

2/ የሽርክና ማኅበሩ ወይም ኩባንያው ቢያንስ አንድ ቡድን ያለው እና የተሻለ አገልግሎት ለመሥጠት የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት ያለው መሆን አለበት፤

3/ በሽርክና ማኅበር ወይም ኩባንያ እያንዳንዱ ዳይሬክተር፣ የሥራ አስኪያጅ እና ሌላ ሥራ አስፈጻሚ ባለሥልጣን ተቀጣሪው የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ፣ መልካም ጠባይ እና ሥነ ምግባር ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፤

4/ የገቢዎች ቢሮ የሽርክና ማኅበር ወይም ኩባንያ የሚሰጡትን የአገልግሎት ዓይነት እና ብዛት፣ የተገልጋዩን ብዛት በማየት በድርጅቱ ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸውን የታክስ ወኪሎች ቁጥር ሊወስን ይችላል።

10. ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

1/ ማንኛውም የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ፈቃድ ለማውጣት የሚፈልግ ሰው የታክስ ወኪል ፈቃድ እንዲሰጠው ገቢዎች ቢሮ ለዚሁ ዓላማ ባዘጋጀው የጸደቀ ቅጽ በመጠቀም ማመልከት አለበት።

2/ ገቢዎች ቢሮ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ፈቃድ ለማውጣት ላመለከተ ሰው ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ እና ሌሎች መስፈርቶች ማሟላቱን በማረጋገጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ያሳውቃል።

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገጉትን ማሟላት ይኖርበታል።

4/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሙያ ፈቃድ በመሆኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚሁ የሥራ መስክ የንግድ ሥራ ፈቃድ ተሰጥቶት እንደሆነ በዚህ ፈቃድ ሥራውን የሚሠራው በታክስ ወኪልነት ብቻ ነው።

5/ በገቢዎች ቢሮ የተሰጠ የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ ተፈጻሚ የሚሆነው በክልሉ ውስጥ ብቻ ይሆናል።

6/ ገቢዎች ቢሮ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሰጣቸውን ሰዎች ዝርዝር አመቺ ሆኖ ባገኘው መንገድ በየጊዜው ይፋ ያደርጋል።

7/ ገቢዎች ቢሮ የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ የሰጠው ግለሰብ ወይም ድርጅት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ከሚሰጣቸው ሰዎች ጋር የተዋዋለውን ሕጋዊ የውል ማስረጃ ለገቢዎች ቢሮ ማቅረብ አለበት።

11. የታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለማደስ

1/ ማንኛውም የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲታደስለት የሚፈልግ የታክስ ወኪል የታክስ ወኪል ፈቃድ እንዲታደስለት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ አገልግሎት ጊዜ ካበቃ በኋላ ባሉት 21 ቀናት ወይም ገቢዎች ቢሮ በሚፈቅደው ጊዜ ከሁለቱ በዘገየ ጊዜ ውስጥ

ገቢዎች ቢሮ ለዚሁ ዓላማ ባዘጋጀው የጸደቀ ቅጽ በመጠቀም ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ማሳደስ ያልቻለ ታክስ ወኪል የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜ ከአበቃበት ቀን ጀምሮ እስከ 6 ወር ድረስ ገቢዎች ቢሮ ታክስ ወኪሉን ተቀብሎ ፈቃዱን ሊያድስለት ይችላል፡፡

3/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከተሰጠበት ወይም ከታደሰበት ጊዜ ጀምሮ ለሦስት ዓመታት የሚጸና ሲሆን በየሦስት ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው ወኪሉ ወይም ተቀጣሪው በገቢዎች ቢሮ እውቅና በተሰጠው ተቋም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ሥልጠና መውሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

5/ ለዚህ አንቀጽ 10 እና 11 አፈጻጸም ገቢዎች ቢሮ በራሱ የሚሰጠውን ወይም በገቢዎች ቢሮ የተወከሉ ድርጅቶች የሚሰጡትን የሥልጠና ዓይነት እና ይዘት ይወስናል፡፡

12. <u>የታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመሰረዝ</u>

1/ የታክስ ወኪልነት ሥራው በጊዜያዊነት እንዲቋረጥ የፈለገ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሥራውን ከማቋረጡ በፊት በ7 (በሰባት) የሥራ ቀናት ውስጥ የሚያቋርጥ መሆኑን ለገቢዎች ቢሮ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም የታክስ ወኪል ፈቃድ በጊዜያዊነት ሊቋረጥ የሚችለው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው፡፡

3/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው በቋሚነት በታክስ ወኪልነት መሥራት ካልፈለገ የታክስ ወኪልነት ፈቃዱ እንዲሰረዝለት ለገቢዎች ቢሮ በጽሑፍ ማመልከት ይችላል፡፡

4/ ገቢዎች ቢሮ ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ መሰረዝ ይችላል፡-

ሀ) ፈቃድ በተሰጠው የታክስ ወኪል ተዘጋጅቶ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ በማንኛውም መሠረታዊ ጉዳይ ሐሰት ሆኖ ሲገኝ፤

ለ) የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱን ለማግኘት የሚጠየቁ እና የሚያስፈልጉ የብቃት መስፈርቶችን ይዞ መቀጠል ሳይችል የቀረ እንደሆነ ወይም

ገቢዎች ቢሮ የታክስ ወኪሉ ሙያዊ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈጽሟል ብሎ ሲያምን፤

ሐ) የታክስ ወኪሉ የታክስ ወኪልነት ሥራውን መሥራት ሲያቆም፣ እንዲሁም የታክስ ወኪሉ ኩባንያ ወይም የሽርክና ማኅበር ሲሆን የኩባንያው ወይም የሽርክና ማኅበሩ ሕልውና ሲያከትም፤

መ) የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱ እንዲሰረዝለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ማመልከቻ ሲያቀርብ፤

ሠ) የታክስ ወኪሉ የፈቃድ አገልግሎት ጊዜ ሲያበቃ እና የታክስ ወኪሉ ፈቃዱ እንዲታደስለት ማመልከቻ ሳያቀርብ ሲቀር እና በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 5 በተደነገገው የጊዜ ገደብ ካልታደሰ ፈቃዱ ይሰረዛል።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ገቢዎች ቢሮ የታክስ ወኪሉ ፈቃድ የተሰረዘ መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ወኪሉ በመስጠት ለሕብረተሰቡ በሚያመች መንገድ ስለመሰረዙ ይፋ ማድረግ አለበት።

6/ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ መሰረዝ የሚጸናው፦

ሀ) የታክስ ወኪሉ የታክስ ወኪልነት ሥራውን መሥራት ካቆመበት ቀን፤ ወይም

ለ) ፈቃዱ የተሰረዘ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ለታክስ ወኪሉ ከተሰጠ ከ60 (ከስልሳ) ቀናት በኋላ፣ ከሁለቱ ቀድሞ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

7/ የገቢዎች ቢሮ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ሙያዊ የሥነ-ምግባር ጥሰት ፈጽሟል ብሎ ሲያምን ይህንን የሥነ-ምግባር ጥሰት፦

ሀ) ለኢትዮጵያ የተመሰከረላቸው የሒሳብ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት፤ ለኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ወይም እንደ አግባብነቱ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሒሳብ ባለሙያነት፣ የኦዲተርነት ወይም የሕግ ባለሙያነት ፈቃድ ለሰጠው ሌላ አካል፤ እና

ለ) የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ኃላፊነት ላለው ባለሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል።

8/ ለዚህ መመሪያ አንቀጽ 10፣ 11 እና 12 አፈጻጸም የገቢዎች ቢሮ የደንበኞች አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ መስጠት፣ ማደስ እና መሰረዝ ሥራን ተግባራዊ የሚያደርግ ይሆናል።

ክፍል ሦስት

የታክስ ወኪሎች ሥልጠናን ስለመወሰን

13. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለመስጠት ለሚያስችል ሥልጠና ጥሪ ስለሚቀርብበት ሂደት

1/ ገቢዎች ቢሮ በየጊዜው በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት ዝቅተኛውን የተፈላጊ ችሎታ መስፈርቶቹን አሟልቶ የሚያቀርብ ማንኛውንም የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ተመዝጋቢ ለሥልጠና ይመለምላል።

2/ በታክስ ወኪልነት የሙያ ሥልጠና ለመሳተፍ ለሚፈልግ ጥሪ ለማድረግ በገቢዎች ቢሮ መምሪያዎች ወይም ጽሕፈት ቤቶች ወይም ውክልና ከተሰጠው ተቋም ከሚለጠፍ ማስታወቂያ በተጨማሪ ገቢዎች ቢሮ ጥሪው አገራዊ ሥርጭት ባለው መገናኛ ብዙኃን (ጋዜጣ፣ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን) እንዲነገር ያደርጋል።

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረቡት አመልካቾች ብዛት ከማሰልጠኛ ተቋሙ አቅም በላይ ከሆነ ገቢዎች ቢሮ በተመዘገቡበት ቅደም ተከተል መሠረት ሥልጠናውን እንዲያገኙ ያደርጋል።

4/ በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት ቢኖሩም ገቢዎች ቢሮ የታክስ ወኪል ለማሰልጠን ፈቃድ በተሰጠው ተቋም ምልመላው እና ሥልጠናው እንዲሰጥ ማድረግ ይችላል።

14. የታክስ ወኪልነት ስለሚያካትታቸው የሥልጠና ርዕሶች

1/ ገቢዎች ቢሮ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ሥልጠና የሚያካትታቸውን የሥልጠና ዓይነቶች እና ርዕሶች ይወስናል።

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሠረት የተመዘገበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ገቢዎች ቢሮ በሚወስናቸው የሥልጠና ርዕሶች ቢያንስ ለ240 ሰዓት ሥልጠና መውሰድ ይጠበቅበታል።

3/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 መሠረት የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማደስ የሚቀርብ በገቢዎች ቢሮ በሚወሰነው የሥልጠና ርዕስ ቢያንስ 120 ሰዓት ሥልጠና መውሰድ ይኖርበታል።

15. <u>የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማውጣት ስለሚሰጥ ፈተና</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 መሠረት የታክስ ወኪልነት ሥልጠና ወስዶ ያጠናቀቀ ማንኛውም ሰው የጽሑፍ ፈተና ይሰጠዋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የጽሑፍ ፈተና የወሰደ ሰው የታክስ ወኪልነት የሙያ ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ለማግኘት ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ማምጣት ይኖርበታል።

3/ ገቢዎች ቢሮ ለታክስ ወኪልነት የሚሰጠውን ፈተና ይዘት ይወስናል።

4/ እያንዳንዱ ሰልጣኝ ለሥልጠናው የሚከፍለው የገንዘብ መጠን በየሥልጠናው ወቅት በታክስ ባለሥልጣኑ የሚወሰን ይሆናል።

5/ ለዚህ መመሪያ አንቀጽ 13፣ 14 እና 15 አፈጻጸም የገቢዎች ቢሮ የግብር ትምህርት እና ኮሙኒኬሽን ዋና የሥራ ሂደት በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የታክስ ወኪል ምልመላ፣ የሥልጠና ርዕሶች መለየት፣ የሰልጣኞች የክፍያ የገንዘብ መጠን እና የፈተና ይዘቱን የመወሰን ሥራዎችን ወይም ሥራን ተግባራዊ የሚያደርግ ይሆናል።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የታክስ ወኪል የሥነ ምግባር መርሆች እና አስተዳደራዊ ጥፋት</u>

16. <u>የታክስ ወኪል የሚመራበት የሥነ ምግባር መርህ</u>

ማንኛውም የታክስ ወኪል፦

1/ በታማኝነት ማገልገል፤

2/ ራስን ከጥቅም ግጭት ማግለል፤

3/ ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፤

4/ ሕግን ማክበር እና ማስከበር፤

5/ ምሥጢር መጠበቅ፤

6/ ለሙያው ብቁ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡

17. ፈቃድ የተሰጠው የታክስ ወኪል ኃላፊነት

1/ የሁሉንም ደንበኞቹን ስም፣ ከደንበኞቹ ጋር የፈጸመውን የሥራ ውል፣ የደንበኞቹን ቋሚ፣ የፖስታ ወይም ሌሎች አስፈላጊ አድራሻዎች፣ ደንበኞቹ የተሰማሩበትን የንግድ ወይም የሥራ ዓይነት የያዘ መረጃ፤ እና

2/ ከዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተጨማሪ የመጨረሻው የታክስ ተመላሽ ወይም የታክስ ማስጠንቀቂያ ለተገልጋዩ የተሰጠበትን ቀን፣ የተከፈለውን ወይም የሚከፈለውን ታክስ ደረሰኝ እና ሌሎች መረጃዎች የያዘ ቋሚ መዝገብ የመያዝ እንዲሁም ገቢዎች ቢሮ የሚጠይቃቸውን ሌሎች መረጃዎች መያዝ እና በገቢዎች ቢሮ ሲጠየቅ ማቅረብ አለበት፡፡

18. ለሥራው የሚያስፈልገውን የመድን ዋስትና ስለመወሰን

በታክስ ወኪልነት ለመሰማራት የሚያስችለውን ፈተና በብቃት የተወጣ የታክስ ወኪል በሚከተለው አኳኋን የመድን ዋስትና ማቅረብ አለበት፡-

1/ የሽርክና ማኅበር ወይም ኩባንያ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሚያወጣ ከሆነ ለደረጃ አንድ የታክስ ወኪል ፈቃድ ብር 150,000 (አንድ መቶ ሀምሳ ሺህ ብር)፣ ለደረጃ ሁለት የታክስ ወኪል ፈቃድ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር)፤

2/ ግለሰብ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሚወጣ ከሆነ ለደረጃ አንድ የታክስ ወኪል ፈቃድ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር)፣ ለደረጃ ሁለት የታክስ ወኪል ፈቃድ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር)፤

3/ ገቢዎች ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰውን የመድን ዋስትና የገንዘብ መጠን እንደ አስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

19. የአሠራር ሥርዓት ስለመዘርጋት

ገቢዎች ቢሮ ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የሚረዳ የአሠራር ሥርዓት ወይም አደረጃጀት ሊዘረጋ ይችላል፡፡

20. <u>የተሻሩ መመሪያዎች</u>

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም አሠራር በዚህ መመሪያ ተሸሯል።

21. <u>የመመሪያው ተፈጻሚነት</u>

1/ ይህ መመሪያ ከሕዳር 8 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትሕ ቢሮ ተመዝግቦ በገንዘብ ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

ባህር ዳር

ጥላሁን መሀሪ አንተነህ (ዶ/ር)

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ኃላፊ